# ግልጽ ደብዳቤ ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም

ውድ ፕሮፌሰር መስፍን፤ በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታችን ይድረስዎ።

ይህ ደብዳቤ የተፃፈው ከቀድሞ ተማሪዎችዎ፤ የሥራ ባልደርቦችዎ፤ ምሁራዊ ሥራዎችዎን ካነበቡና፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) መሥራችና መሪ ሆነው ላደረጓቸው ፈር-ቀዳጅ ሥራዎች፤ አድናቆት ካለን ሰዎች ነው።

ከዚህ በላይ ባጭሩ የገለፅነው ለእርሰዎ ያለን ክብር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከእርሰዎ ጋር ሆነን በኢትዮጵያችን ውስጥ ዲሞክራሲና ሰላም እንዲሰፍን አብረን ስንሰራ የነበርን፤ እርሰዎና ሌሎቹ የፖለቲካ እስረኞች ከእስር እንዲትፈቱ ሌት ተቀን የለፋን ወዳጆችዎ በቅርብ ጊዜ በተፈጠረው ሁኔታ በመቆርቆር የተንሳ ይህንን ግልፅ ደብዳቤ ለመፃፍ ተገደናል።

ጉዳዩ እርሰዎ የሚመሩት "የአንድነት ፓርቲ" ቡድን ከመድረክ ጋር ተቀላቅሎ ከሚሰራው የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የሚያደርገውን ትንንቅ በተመለከ ነው። ግልጽ ለማድረግ ያህል፤ በቅርቡ በኮኮበ ፅባህ ት/ቤት በመጋቤት 29 ቀን 2002 ዓ/ም ያሳለፉችሁትን ውሳኔ በአንክሮ ተመልክተነዋል። እርሰዎም በዚህ እድሜዎ የወ/ሪት ብርቱካ "የወንበር ጠባቂ" ሆኜ ተመርጫለሁ ብለው ያስተላለፉትንም ዜና በመገርም አዳምጠናል። ይህንኑ በተመለከት በየጊዜው የሚጽፏቸውን ጽሁፎች አንብበናል። በእኛ አመለካከት ጽሁፎችዎና የሚሰጧቸው ቃለ-መጠይቆች በቀረጣ መልክ "ምርጫን ማሸነፍ" ተግባሩ ለሆነው ለገኘው ፓርቲ መጠቀሚያ ሆኗል። ይህንን በሚመለከትም እኛ "ምላሽ እናድርግ ወይስ አናድርግ" እያልን ከእራሳችን ጋር ስንሟገት ቆይተናል። እርሰዎና የእርሰዎ ተከታዎች በፀረ-ዲሞክራሲው መንግሥት ላይ ያነጣጠረ ትግል እንደማካሄድ፤ ደርሻችሁን ለጋራ ትግሉ እንደማበርከት ፋንታ፤ በአንፃሩ ግን በዲሞክራሲያዊ ሀሎች ላይ ያነጣጠረ ተኩስ መተኮሳችሁ ታሪካዊ ስህተት ነው።

ይህ በዲሞክራሲያዊ ሀይሎች መካከል የሚደረገው መጠላለፍ ከዛሬ ነገ ይበርዳል ብለን ስንጠብቅ፤ ጣልቃ ላለመግባት ስንልም፤ ታግሠን ቆየን። እርሰዎና ተባባሪዎችዎ እንደጠላት የምትቆጥሯቸውን ሀይሎች "ታገሷቸው" እያልን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምክራችንን ስንለግስ ቆይተናል። ሆኖም ግን ሁኔታው ከፅለት ወደ ፅለት ተባብሶ፤ እንዳውም እስከ ምርጫው ዋዜማ ደርሶ፤ ምንም እንኳ እርሰዎና ተባባሪዎችዎ የምታደርጉት ከፀረ-ዲሞክራሲ ሀይሎች ጋር የሚደረገውን ትንንቅ ያዳክመዋል ብለን ባንጠብቅም፤ በአንድ በኩል በአሁኑ ጊዜ ከእርሰዎ የሚጠበቀው አደናጋሪና ከፋፋይ ተግባር ሳይሆን፤ ከፍተኛ ትግስትን ተመርኩዞ፤ የተጣሉትን ማስታረቅ፤ ያለተስማሙትን ማስማማት ስለሆነ፤ በሌላ በኩል ደግም በአሁኑ ጊዜ የዓላማ አንድነት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች የሚያደርጉትን የመፈላልግ እንቅስቃሴን እርሰዎና ተባባሪዎችዎ ይህንን መልካም ተግባር የሚቃረንም ስለሆነ፤ ይህንኑ ተገንዝበው በስቸቋይ እንዲያስተካክሉ እንጠይቃለን።

በመጨረሻም፤ ይህንን ግልጽ ደብዳቤ የላክነው ምሁራን ስማችንን አሁን በይፋ ለመግልፅ ያልፈለግንበት ዋናው ምክንያት ከላይ እንደገለፅነው፤ የእርሰዎ አጋሮች ስለሆንን፤ ጊዜውና ሁኔታው ባመቸ ጊዜ ከእርሰዎ ጋር ውይይት ለመቀጠል እንዲያመቸንና የኢትዮጵያ ሕዝብም የስህተቱ ሰለባ እንዳይሆን በማሰብ ነው።

ካክብሮት ጋር፤

በሁኔታው የተቆረቆርን በውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ምሁራን።